2016-05-03

*Smittskyddsläkarnas smittskyddsblad*

# ኤችአይቪ

የበሽተኞች መረጃ: መብቶችና ያግባብ መመሪያዎች። በኢንፌክሽን ሀኪም የሚሠጥ የበሽታ መረጃ ቅጠሊት።

## ይህ መረጃ ለምን ወደርስዎ ተላከ?

ይህ መረጃ የተላከልዎት ምክንያት የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ስላለዎት ወይም እንዳለዎት ጥርጣሬ ስላለ ነው። ይህ ቅጠሊት: ኤችአይቪን የሚመለከት መረጃ: እንዴት ህክምና እንደሚሠጥና ምን ማድረግ እንዳለብዎት የሚገልጽ መረጃ ያጠቃለለ ነው።

## ኤችአይቪ ምንድነው?

ኤችአይቪ በሰው አካል በሽታ የመቋቋም ሀይል (ኢሚዩን ሲስተም) ላይ ተጽኖ የሚያደርግ ቫይረስ ነው። ዛሬ በተገቢ አግባብ ከተወሰዱ በሰው አካል ያለው የቫይረስ መጠን የሚቀንሱና፤ በኤችአይቪ የተለከፉ ሰዎች ረጅምና ጥሩ ህይወት እንዲያሳልፉ የሚያስችሉ መድሃኒቶች አሉ። መድሃኒቶቹ በተገቢ አግባብ ከተወሰዱ ለሌላ ሰው ኤችአይቪ የማስተላለፍ አደጋ በጣም ነው የሚቀንሰው።  የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ድኖ አይጠፋም፤ በሽተኛው በጥሩ አግባብ መድሃኒት ቢወስድም በአካሉ ቫይረስ ይኖራል። አንድ በኤችአይቪ የተለከፈ ሰው ህክምና ካልወሰደ: ቆየት ብለው ያልተለመዱ ኢንፌክሽኖችና የካንሰር በሽታ ይነሡበታል። ይህ ቆይቶ የሚነሣው ክስተት ኤይድስ ይባላል። አብዛኞቹ ዛሬ የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ያላቸው ሰዎች: በመጪው ጊዜ በፍጹም ኤይድስ አይነሣባቸውም።

## ኤችአይቪ እንዴት ይተላለፋል?

አብዛኞቹ በኤችአይቪ የተለከፉት ግለሰዎች: የብልት: የፊንጢጣና አንዳንድ ጊዜም የአፍ ወሲብ ካለ መከላከያ በመፈጸማቸው ነው። በኤችአይቪ ቫይረስ የተበከለ ደም: ከሰው ወደ ሰው በሽታ የማስተላለፍ አደጋው ትልቅ ነው። በዚህ ምክንያት ኤችአይቪ በስግረ-ደም: በመርፌ ወይም በሌላ መውግያ መሳሪያ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል። በኤችአይቪ ቫይረስ የተበከለ ደም በዐይን: ባፍንጫና: በአፍ ካለው የንፋጭ ገለፈት ወይም ክፍት ከሆነ ቁስል ጋር ቢገናኝም የመለከፍ አደጋ አለ። የኤችአይቪ ህክምና በተገቢ አግባብ ከተከናወነ: የመተላለፍ አደጋው እጅግ በጣም ቢቀንስም፤  የመለከፍ አደጋው ግን ያው እንዳለው ነው። ኤችአይቪ በእርግዝና: በግልግልና በማጥባት ወቅት ከእናት ወደ ልጅ ሊተላለፍ ይችላል። እናቲቱ የኤችአይቪ ተሸካሚ መሆንዋ እውቅ ከሆነ: በመድሃኒትና ልጁን ባለማጥባት ወደ ልጁ ቫይረስ ለማስተላለፍ ያለውን አደጋ ከተቻለ እስከ ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ይቻላል።

## ኤችአይቪ መቸ ከሰው ወደ ሰው ይተላለፋል?

ኤችአይቪ በመተቃቀፍ: በመሳሳምና በመተሻሸት አይተላለፍም። እንባ: ሽንት: ተቅማጥ: ትውከት ወይም ንፍጥ: ደም እስካልተቀላቀለበት ድረስም ኢንፌክሽን አያስተላልፍም። ባልቆሰለ ቆዳ የነጠበ ደምም የማስተላለፍ አደጋ የለበትም።

## መብቶች

በስዊድን የኢንፌክሽን ህግ (smittskyddslagen) መሠረት: ምርመራ: የሀኪም ቀጠሮና: ህክምና ለሁሉም በሽተኞች ከክፍያ ነፃ ነው። በሽታዎን ለመቻል የሚያስፈልግዎት ስነ-አእምሮአዊና ማህበራዊ ደገፍ የማግኘት መብትም አለዎት። ሌሎች ሰዎችን በኢንፌክሽን አደጋ ላይ እንዳያጋልጡ ማስወገድ የሚገባዎትን ነገሮች በሚመለከት የኢንፌክሽን ሀኪምዎ ምክር ይሠጥዎታል። የኤችአይቪ ኢንፌክሽን ተሸካሚ በመሆንዎ ብቻ መብትዎ መደፈር የለበትም። ኤችአይቪ በስዊድን የፀረ-ዘረኝነት ህግ ውስጥ ከሚገኘው የአቅመ-ውሱንነት ዓምድ ላይ ሰፍሮ ይገኛል።

## የሙያ ኑሮ

የኤችአይቪ ኢንፌክሽን: ትምህርትዎና ደምበኛው የሙያ ኑሮዎ ለማከናወን አይከለክልዎትም።

## እርግዝናና ልጅ ማጥባት



***smittskyddsenheten***

Centrallasarettet, 351 85 Växjö. ☎0470-588278

ልጅዎ ሳይለከፍ ባነስተኛ የኢንፈክሽን አደጋ: እርጉዝ መሆን ይችሉ ዘንድ: እርስዎ/የኑሮ ጓደኛዎ ድጋፍ ማግኘት ትችላላችሁ። ኤችአይቪ ተሸካሚ እናቶች ማጥባት የለባቸውም።

**በኤችአይቪ የተለከፉ ልጆች**
ወላጆች/አሳዳጊዎችና ልጆች: ከዕድሜአቸው የሚስማማ: ህክምና በሚሠጠው ሀኪም በኩል በተከታታይ መረጃ ያገኛሉ። በኤችአይቪ የተለከፉ ልጆች ልክ እንደ ሌሎች ልጆች ለእንክብካቤና ለትምህርት መብት አላቸው። ቢሆንም: በግምት ውስጥ የሚገቡ ልዩ ፍላጎቶች ሊኖራቸው ይችላል። ህክምና የሚሠጠው ሀኪም ወይም የኢንፈክሽና መከላከያ ሀኪሙ: ወላጆቹ/አሳዳጊዎቹ ከፈቀዱ: ለዐፀደ-ህፃናቱ መረጃ ሊሠጥ ይችላል። ትምህርት ሲጀምር የትምህርት ቤቱ የተማሪ ጤና ጥበቃ ክፍል (skolhälsovården) ይነገራል።

**የብልት: የፊንጢጣና የአፍ ወሲብ ሲፈፀም ኮንዶም መጠቀም**
ኮንዶም መጠቀም: ኤችአይቪና ሌሎች በወሲብ የሚተላለፉ በሽታዎችን ለመከላከል ማለፊያ የሆነ አግባብ ነው። እና ወሲቡ ተጀምሮ እስኪጨረስ ኮንዶም ጥቅም ላይ መዋል አለበት። የእምስ ኮንዶም (የሴቶች ኮንዶም) ሊጠቅም ይችላል ግን በሳይንስ የተደገፈ መረጃ የለም። ተገቢ ህክምና በሚደረግበት ወቅት በተቻለ መጠን ከሰው ወደ ሰው የኤችአይቪ የመተላለፍ አደጋ ለመቀነስ: የብልት: የፊንጢጣና የአፍ ወሲብ ሲፈፀም ኮንዶም መጠቀም ግዴታዊ ነው።

**ኢንፈክሽን በመከላከል ላይ ያተኮረ የመድሃኒት ህክምና**
በወሲብ ወቅት ኮንዶም ተጠቅመው ሲያበቁ ግን ወደ ሌላ ሰው በደምዎ ወይም በሌላ መልክ ኢንፈክሽን እንዳስተላለፉ ጥርጣሬ ካለ: የድኅረ-መጋለጥ የኢንፈክሽን መከላከያ ህክምና (postexpositionsprofylax (PEP) ማድረግ ይቻላል። ይህ የኢንፈክሽን መከላከያ ህክምናው ወዲያዉኑ መጀመር አለበት። ህክምና ከሚሠጠዎት ሀኪም ወይም ከኢንፈክሽን ክሊኒኩ ኮንታክት ያርጉ።

**የኢንፈክሽኑ ምንጭ መፈለግ**
ተገቢ ህክምና እንዲያገኙና ኢንፈክሽን ወደ ሌሎች ግለሰዎች እንዳይተላለፍ ለመከላከል: ኤችአይቪ ያላቸው ግለሰዎች ማግኘት (እነማን መሆናቸው ማወቅ) በጣም አስፈላጊ ነው። እና የኤችአይቪ ተሸካሚ ከሆኑ: ከማን ወይ ከነማን ኢንፈክሽኑ እንደተላለፈብዎት ወይም እርስዎ ያስተላለፉበት ግለሰው ካለ የመንገር ግዴታ አለብዎት። ይኸም ማለት: ከርስዎ ወሲብ ወይም ሌላ ዓይነት ግኑኝነት የፈፀሙ ግለሰዎች ወይም የመውግያ መርፌ መሳይ ከርስዎ የተጋሩ: አንዳንድ ጊዜም የቤተሰብ አባሎችን የሚመለከት ሊሆን ይችላል። ይህ የኢንፈክሽን ዋና ምንጭ የማግኘት ተልእኮ የሚመራው: በበሽተኞች መቀበያ ያለው ህክምና የሚሠጥዎት ሀኪም: ተጋጋኙ (kurator) ወይ ነርስ ነው። ለምንጭ ፈላጊው የሚነግሩት መረጃ ሁሉ በምስጢር (sekretess) ነው የሚያዘው። መረጃ ሲሠጡ እርስዎ የሚጠቅሷቸው ግለሰዎች እርስዎ ማን እንደሆኑ አያውቁም። ግለሰዎቹ በሀኪም መመርመር እንዳለባቸው ብቻ ነው የሚነገራቸው።

**ደም ሁልጊዜ እንደ አደገኛ የኢንፈክሽን ማስተላለፊያ መንገድ መታየት አለበት**
- *ቁስል ወይም ሌላ ተመሳሳይ ነገር አዲስ መሸፈኛ ሲደረግበት ደም የሚነካ ግለሰው ጓንቲ ማድረግ አለበት።*
- *በደም የቆሸሸ ማተርያል (ጨርቅ ወዘተ.) ከመጣሉ በፊት መታሸግ አለበት። ልብስ በማሽን መታጠብ አለበት።*
- *አንድ ግለሰው: ዐይኑ: አፍንጫው ወይም አፉ ውስጥ ደም ከገባበት ወዲያዉኑ በውሃ ማታጠብ/መጉመጥመጥ አለበት። ደሙ ኤችአይቪ እንዳለበትና ግለሰዉ ህክምና ከሚሠጥ ሀኪም ወይም ከኢንፈክሽን ክሊኒክ ጋር ወዲያዉኑ ኮንታክት ማድረግ እንዳለበት የመንገር ግዴታ አለብዎት።*

**ወደ ሌላ ግለሰው ኢንፈክሽን ላለማስተላለፍ ሊከተሏቸው የሚገባዎት መመሪያዎች**
በኢንፈክሽን መከላከያ ህግ መሠረት: ኤችአይቪ ለህዝብ አደገኛ የሆነ (allmänfarlig sjukdom) በሽታ ነው። እና ኢንፈክሽን ወደ ሌላ ሰው እንዳይተላለፍ ለማስወገድ እርስዎም ኃላፊነት ይሸከማሉ። የኤችአይቪ ኢንፈክሽን የማስተላለፍ አደጋ ከተከሰተ: ግለሰዉን ስለ በሽታዎ የማሳወቅ ኃላፊነት አለብዎት። በህግ

የሚጠቀሱት ጉዳዮች መሠረት በማድረግ: ከዚህ ቀጥለው የኢንፈክሽን መተላለፍ የሚያስወግዱ መመሪያዎች ተዘርዝሯል። አብዛኞቹ መመሪያዎች ለኤችአይቪ ተሸካሚዎች ሁሉ የሚመለከቱ ሲሆኑ: የተቀሩት ግን እርስዎ ባሉበት ሁኔታ የተመሠረቱና ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊቀያየሩ የሚችሉ ናቸው። ከተዘረዘሩት መመሪያዎች የትኞቹ እርስዎን እንደሚመለከቱ የሚወሥነው ሀኪምዎ ነው።

1. *የኢንፈክሽን መተላለፍ አደጋ ባለበት ወቅት: በሥራ ወይም በሌላ እንቅስቃሴ የመሳተፍ ክልከላ ሊያጋጥም ይችላል።*
2. *ደም ይሁን የሰውነት ክፍል ለስግረት (transplantation) መለገስ አይፈቀድልዎም።*
3. *ለህክምና የተጠቀሙበት የመርፌ ጋን ወይም ሌላ ተመሳሳይ መርፌ ለሌላ ሰው መሥጠት አይፈቀድልዎትም።*
4. *አደንዛዥ ዕፆች ለመውሰድ የተጠቀሙበት (የሚወስዱ ከሆነ) የመርፌ ጋን ወይም ሌላ ተመሳሳይ መርፌ ለሌላ ሰው መሥጠት አይፈቀድልዎትም። ከሌላ ሰው የአደንዛዥ ዕፅ መቀላቀያ ኩባያ በጋራ መጠቀም እንዲሁም አይፈቀድልዎትም። ሁሉም አደንዛዥ ዕፅ ለመውሰድ የሚያገለግል መሣሪያ: ለኢንፈክሽን መተላለፍ አደጋ ላይ በማይጥል አግባብ መቀመጥ ወይ መጣል አለባት።*
5. *የጥርስ ህክምና ወይም ሌላ ህክምና ሲያደርጉ እና የህክምና ሠራተኞች ደምዎን የሚነኩ ከሆነ: (ለምሣሌ ደም ሲሥጡ ወይም ቀዶ ጥገና ሲደረግልዎት) ደምዎ በኤችአይቪ እንደተበከለ በግድ ማሳወቅ አለብዎት።*
6. *መነቀስ ወይም ጆሮዎን መበሳት ከፈለጉ: ወይም ሌላ ሹል ነገር የሚጠቀሙበት ወቅት ኖሮ የመድማት አደጋ ካለ (ለምሳሌ "ፒርሲን" (piercing) በሚደረግበት ወቅት): ጉዳዩ ከመጀመሩ በፊት አስቀድመው በደም የሚተላለፍ በሽታ እንዳለብዎት የግድ ማሳወቅ አለብዎት።*
7. *ለኤችአይቪ መተላለፍ አደጋ ላይ ሊዳርግ የሚችል የወሲብ ግኑኝነት ከማድረግዎ በፊት: የወሲብ ጓደኛዎን የኤችአይቪ ተሸካሚ መሆንዎን በግድ ማሳወቅ አለብዎት። የብልት: የፊንጢጣና የአፍ ወሲብ በሚደረግበት ወቅት የመተላለፍ አደጋ አለ። ወሲብ በሚደረግበት ወቅት ኮንዶሙ ሊቀደድ ስለሚችል: ኮንዶም ለመጠቀም በሚመድቡበት ወቅትም እንዲሁ ኤችአይቪ እንዳለብዎት በግድ ማሳወቅ አለብዎት። የወንድ ብልት በሴት ብልት በሚገባበት ወቅት: የወንድ ብልት በፊንጢጣ ወይም በአፍ በሚገባበት ወቅት ኮንዶም መጠቀም አለብዎት። በሌላ ዓይነት ወሲብ የእምስ ኮንዶም (የሴት ኮንዶም) መጠቀም ይገባል። በተገቢ የሚደረግ ህክምና ቢያደርጉም የእምስና የፊንጢጣ ወሲብ በሚፈፀምበት ወቅት ኮንድም በግድ ይጠቀሙ።*
8. *እንደ ምላጭ: የጥርስ መፋቂያና ሌሎች የማጠቢያ ቤት ዕቃዎች ከሌሎች መጋራት አይፈቀድልዎትም።*
9. *ሀኪምዎ አስፈላጊ ነው ብሎ በወሠነልዎት ቀጠሮ በግድ መገኘት አለብዎት።*

ስህተተኛ ነው ብለው የሚገምቱት መመሪያ ከተሠጠዎት: ባሉበት ላንድስቲን (landsting) የሚገኝ የኢንፈክሽን መከላከያ ሀኪም ያነጋግሩ።


**_smittskyddsenheten_**
Centrallasarettet, 351 85 Växjö. ☎0470-588278